# <u>የአማርኛ ትምህርት የፈተና መለማመጃ ጥያቄዎች</u>

## <u>ክፍል ሁለት</u>

1. ዋ! አበባዉን እንዳትቆእጡ ፡፡ ይህ ዓረፍተ ነገር ስልቱ ምንድን ነው ?

   ሀ) መጠይቅ　　ለ) ትዕዛዛዊ　　ሐ) አጋኖአዊ

2. ህጻኑ **<u>ዱባ</u>** ስለሆነ ለማንሳት ከበደኝ፡፡ የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ፡

   ሀ) ዱባ ወጥ ስለሚበላ　　ለ) ወፍራም　　ሐ) ክሲታ

3. ጠዋት የወጣሁ **<u>እንጀራ</u>** ፍለጋ ስንከራተት ዋልኩ ፡፡ ለተሰመረበት ቃል ፍቺ

   ሀ) ምግብ　　ለ) ስራ　　ሐ) ጉዳይ　　መ) እንጀራ ጋገራ

4. **<u>ቁጤማ</u>** የሚለው ቃል እማሬያዊ ፍቺ፡

   ሀ) ልፍስፍስ　　ለ) የሳር አይነት　　ሐ) ቀጭን　　መ) ረጅም

5. **<u>ጎመን</u>** የሚለው ቃል ፍካሬያዊ ፍቺ፡

   ሀ) የማይሰማ　　ለ) አቅመ ቢስ　　ሐ) የቅጠል አይነት　　መ ) ሀ እና ለ

6. ከሚከተሉት ውስጥ ተገብሮ ዓረፍተ ነገር የቱ ነው?

   ሀ) ተተከለ　　ለ) ሰረቀኝ　　ሐ) ተከለ　　መ) ተከሉ

7. **<u>ሚጥሚጣ</u>** ለሚለው ቃል እማሬያዊ ፍቺ፡

   ሀ) የሚያቃጥል　　ለ) ለፍላፊ　　ሐ) ዝምተኛ　　መ) ቀይ

8. የተራኪ ፅሁፍ አቀራረብ ምንን ያካትታል?

   ሀ) ክስተቶችን　　ለ) አፈፃፀም　　ሐ) ሁሉም

9. ሀይለኛ ራስ ምታት ስለያዘኝ ከትምህርት ቤት ቀረሁ ፡፡ የዚህ ዓረፍተ ነገር ውጤት ምን ይሆናል?

   ሀ) ራስ ምታት　　ለ) ከ ት/ቤት መቅረት　　ሐ) መያዝ

10. ተህዋሲያን ምንድን ናቸው?

    ሀ) በሽታ አምጪ　　ለ) በሽታ　　ሐ) አልሚዎች

LIVEWORKSHEETS

11. ድንቁ ሁልጊዜ ከሃብታሞች **አራጣ** መውሰድ አይሰለቸውም:: ለተሰመረበት ቃል አገባባዊ ፍቺ የሚሆነው:

ሀ) ድህነት ለ) ፀጋ ሐ) ብድር መ) ሽዕቀጥ

12. አቶ ሙሳ በቀጥታ ከመናገር ይልቅ **በአግቦ** መናገርን ይመርታል። ለተሰመረበት ቃል ተመሳሳይ ፍቺ ሊሆን የሚችለው፤

ሀ) በተረት ለ) በአሽሙር ሐ) በምሳሌ መ) በጩሀት

13. አበበ ስራው ሁሉ **ጣዕመቢስ** ነው ሲል ለተሰመረበት ቃል ተቃራኒያዊ ፍቺ ሊሆን የሚችለው:

ሀ) ለዛያለው ለ) ለዛቢስ ሐ) አሰልቺ መ) ያማይጥም

14. **እንደማይመጣ** ከሚለው ቃል ሊመሰረቱ የሚችሉት ቃላት የትኞቹ ናቸው?

ሀ) ማደን፣ መጣ፣ ጣመ፣ ማን፣ ደን

ለ) ደን፣ ማዳን፣ መጣ፣ ጣመ

ሐ) መጣ፣ ማደን፣ ደን፣ ይምጣ

መ) ደመና፣ ማይ፣ ደን፣ ደናማ

15. የትምህርትቤታችን ርዕሰ መምህር **አንደበተ ስል** ነው ሲባል ምን ለማለት ተፈልጎ ነው ?

ሀ) ቋንቋ ስለተማረ ሲናገር ያምራል

ለ) አንደበተ ርቱዕ እና አስተዋይ ነው

ሐ) ድምጹን ከፍ አድርጎ ይናገራል

መ) የንግግር አንደበቶቹ ያምራሉ

16. **ዛጎል አይን** ለሚለው ፈሊጣዊ ንግግር ተመሳሳይ ትሩም ሊሆን የሚችለው

ሀ) ትናንሽ አይን ለ) ትልልቅ አይን

ሐ) ዐይኑ ላይ የጣለበት መ) ሸውራራ

17. ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ድርብ ቃል ያልሆነው የቱ ነው ?

ሀ) አጸደ ህፃናት ለ) ትምህርት

መ) ስር ዓተ ትምህርት መ) አገር ቤት

LIVEWORKSHEETS

18. ከሚከተሉት መካከል **ቋንጣ** የሚለው ቃል በፍካሬያዊ ፍች የተገለጸው በየትኛው አማራጭ ነው ?

ሀ) ተዘልዝሎ የደረቀ ስጋ ለ) በገመድ ላይ የሚሰቀል የስጋ አይነት

ሐ) ለምግብነት የሚያገለግል ደረቅ ስጋ መ) ቀጭን ወይም ከሲታ ሰው ማለት ነው

19. ከሚከተሉት አማራጮች ስለ እማሬያዊ ፍች ትክክል የሆነው:

ሀ) አገባባዊ ፍች ማለት ነው ለ) መዝገበ ቃላዊ ፍች ማለት ነው

ሐ) ቀጥተኛ ፍች ማለት ነው መ) ለ እና ሐ

20. ከሚከተሉት መካከል ግስን በትክክል ሊገልጽ የማይችለው የቱ ነው?

ሀ) እየ የሚል ቅድመ ቅጥያ ምዕላድን ይወስዳል ለ) በግዕዝ ፊደል ይጀምራል

ሐ) በአረፍተ ነገር መጨረሻ ይመጣል መ) አብዥ ምዕላዶችን ይወስዳል

21. መልካም ሴት .............

ሀ) ለባሏ ዘውድ ናት ለ) ጥሩ ቁመና አላት

ሐ) ባለሙያ ናት መ) ሁሉም

22. መልካም ምላስ ............

ሀ) ደግ ታወራለች ለ) ቁጣን ታበርዳለች

ሐ) መልካም ታደርጋለች መ) ሁሉም

23. ሳያጣሩ ወሬ.................

ሀ) አለመናገር ለ) ሳይገሉ ጎፈሬ

ሐ) ውሸት ነው መ) ሁሉም

24. አፍ ሲያመልጥ................

ሀ) አያስታውቅም ለ) እራስ ሲመለጥ አያስታወቅም

ሐ) ያስደነግጣል መ) ያሳፍራል

25. ነገር ቢበዛ .............

ሀ) ያሰለቻል ለ) በአህያ አይጫንም

LIVEWORKSHEETS

ሐ) መፍትሔ የለውም　　　　መ) መ/የለም

26. ውሀ ቢወቅጡት .............

ሀ) አይደንቅም　　ለ) እንቦጭ　　ሐ) ጥቅም የለዉም　　መ) ሀ እና ሐ

27. በጊዜ ቅደም ተከተል ስላለፈ ድርጊት የሚተርክ ወይም የሚያትት ጽሁፍ ምን አይነት ድርሰት ተብሎ ይጠራል?

ሀ) ተራኪ ድርሰት　　ለ) አመዛዛኝ ድርሰት

ሐ) ገላጭ ድርሰት　　መ) ስዕላዊ ድርሰት

28. **ኣት** የሚለውን አብዥ ምዕላድ የሚወደው ቃል የቱ ነው ?

ሀ) ደራሲያን　　ለ) ጸሃፊያን　　ሐ) ተዋኒያን　　መ) ሰማያት

29. **<u>ነት</u>** የሚል ቅጥያ ተጨምሮበት የሚታየው በየትኛው ቃል ላይ ነው?

ሀ) መቀነት　　ለ) ልጅነት　　ሐ) እውነት　　መ) ሁሉም

30. ከሚከተሉት ውስጥ በአራት ምዕላድ ሊከፋፈል የሚችለው የትኛው ነው ?

ሀ) እንደአባቶቻችን　　ለ) ስለወንዞችን

ሐ) ከመንደራችን　　መ) ጎረቤቶቻችን

31. ሆድ ያባውን............................................ የዚህን ፈሊጣዊ ንግግር ሊያሟላ የሚችለው:-

ሀ) አፍ ያወጣዋል　　ለ) አፍ ይተፋዋል

ሐ) ብቅል ያወጣዋል　　መ) ማን ያውቀዋል

32. የላጭን ልጅ............................................ የዚህን ፈሊጣዊ ንግግር ሊያሟላ የሚችለው:-

ሀ) አሳከካት　　ለ) ቅማል በላት

ሐ) ምላጭ የላት　　መ) ምላጭ አላት

33. መልከ ስጠኝ እንጂ................................................. የዚህን ፈሊጣዊ ንግግር ሊያሟላ የሚችለው:-

ሀ) እቃ ከጎረቤቴ　　ለ) ሙያ ምን ይሰራልኝ

ሐ) ሙያው አያስቸግረኝም　　መ) ሙያ ከጎረቤቴ

LIVEWORKSHEETS

34. ከሩቅ ዘመድ...................................... የዚህን ፈሊጣዊ ንግግር ሊያሟላ የሚችለው፡-

ሀ) የቅርብ ጓደኛ

ለ) የቅርብ ጎረቤት

ሐ) የቅርብ ሰው

መ) የቅርብ እህት

35. ከአህያ የዋለች ጊደር ............................................... የዚህን ፈሊጣዊ ንግግር ሊያሟላ የሚችለው፡-

ሀ) ሸከም ተመራ ትመጣለች

ለ) ፈስ ተምራ ትመጣለች

ሐ) ሥራ ተምራ ትመጣለች

መ) መሸከም ትወዳለች

LIVEWORKSHEETS